# አደራዳሪ እባብ ተደራዳሪ ጅብ!




ታሪክ እንደ ጻፈው ትውልድ እንደሚያውቀው፣
በዘንዶና በእባብ በጊንጦች ታግዘው፣
የላምን እረኛ ነድፈው አስወግደው፣
ሰነድን ፈረሙ ጅብና ጥንብ አንሳው፣
ተካፍለው ሊበሏት ላሟን ዘጠኝ አርገው፡፡

በእባብ መካሪነት ደምን ተሚመጠው፣
ለሰላሳ ዓመታት ዘለቁ ተስማምተው፣
ጅቡ ባለስልጣን ጥንብ አንሳ አሽከር ሆነው፡፡

በልቶ እማይጠግብን ጅብ ግፉ ጣለውና፣
ጥንብ አንሶች አረፉት ስልጣኑን ያዙና፡፡

በስልጣን ዘመኑ ሆዱ የሰፋው ጅብ፣
እንዴት ይዋጥለት ዳረጎት መቀበል፣
ጥንብ አንሳ ተሚባል ተድሮው ጥሩ አሽከር፡፡

ጥንብ አንሶች ተጅቡ በስልጣን ተጣልተው፣
ስንት ወይፈን አስፈጁ ላምን አዳኝ መስለው፡፡

ጅብ ሰክሮ ሲመጣ አተላውን ቅሞ፣
ጥንብ አንሳን ሊያወረደው ተስልጣን ዠልጦ፣
ወይፈንና ኮርማ አዳነው ተዋግቶ፣
ለላሚት ጥንብ አንሳው ተጅብ ይሻል ብሎ፡፡

ነገር ግን ጥንብ አንሳ የድሮው ጅብ አሽከር፣
ለጊዜውም ቢሆን ስልጣኑን ሲስያከበር፣
ለጅብ መኖር ሲፈቅድ ተወንዙ ባሻገር፣
መናቆር ጀምረ ተወይፈን ኮርማ ጋር፡፡

ጥንብ አንሳ እርግቦችን ጅብ በግ እንደማይሆን፣
ከሰላሳ ዓመት ውጪ ማን ይንገርህ ወይፈን?

የሰላሳ ዓመቱ ታሪክ ሲመረመር፣
ጀሬ ትርፍራፊ ጉርሻ ለመቀበል፣
ስንቱን ወይፈን ኮርማ በጅብ አስበልቷል፡፡

እባክህ ወይፈን ሆይ ዛሬ እንኳን ነቃ በል፣
ጅብና ጥንብ እንሳ የተጣሉ ቢመስል፣
እውነት አይምሰልህ እንዳትንዘላዘል፣
ለአያሌ ዘመናት በአንድ ማድ በልተዋል፣
ላሚን በጥርስ ነክሰው ደሚን ጠጥተዋል፡፡

እባብና ዘንዶም ሽማግሌ መስለው፣
ጅብና ጥንብ አንሳን እንደገና አስማምተው፣
ለጀሬ አግዳሚውን ለጅብ ወንበር ሰጥተው፣
ምድርን ለላም ልጆች ሲኦል ሊያደርጓት ነው፡፡

አደራዳሪ እባብ ተደራዳሪ ጅብ ሆኖ የሚቀመጥ፣
ከብትን አዘናግቶ ቂጥን ለማስገምጥ፣
ጀሬም እንዳመሉ ትርፍራፊ እንዲውጥ፡፡

ሲመክሩህ ሲዘክሩህ ኮርማ ሆይ ልብ በል፣
ዛሬም የጥንብ አንሳው ተጅብ ጋር ድርድር፣
ላሚን እንደገና በጅብ ለማስወረር፣
መሆኑን አጢነህ አካኬ ዘራፍ በል፣
አንድ ላይ ከትመህ ምክርና ዘክር፣
በቀንድህ በሻኛህ ክብርህን አስከብር፡፡

በላይነህ አባተ ((abatebelai@yahoo.com)
መጀመርያ ታህሳስ ሁለት ሺ አስራ አራት ዓ. ም.
እንደገና ጥቅምት ሁለት ሺ አስራ አምስት ዓ. ም.